የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 6
ADDIS ABABA 25th December,2008

ማውጫ

በአዋጅ ቁጥር ፮፻፱/፪ሺ፩ ዓ.ም

የተጨማሪ እሴት ታክስ /ማሻሻያ/ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፫፻፸፩

CONTENTS

**Proclamation No. 609/2008**

Value Added Tax (Amendment) Proclamation Page 4371

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፱/፪ሺ፩

## <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ /፩/ እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “የተጨማሪ እሴት ታክስ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፱/፪ሺ፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተተክቷል፣

“፬/ “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፣”

## PROCLAMATION NO. 609/2008.

## <u>A PROCLAMATION TO AMEND THE VALUE ADDED TAX PROCLAMATION</u>

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Value Added Tax Proclamation N0. 285/2002;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Value Added Tax (Amendment) Proclamation No. 609/2008”.

**2. <u>Amendment</u>**

The Value Added Tax Proclamation No. 285/2002 is hereby amended as follows:

1/ Sub-Article (4) of Article 2 of the Proclamation is repealed and amended by the following new Sub-Article (4):

“4/ ‘Authority’ means the Ethiopian Revenues and Customs Authority;”

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፳፭/ እና /፳፮/ ተጨምረ ዋል፣

"፳፭/ "የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ" ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው፣

፳፮/ "አቅራቢ" ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ወይም በመሣሪያው ላይ ተጭኖ አገልግሎት የሚሰጥ ሶፍት ዌርን ወይም ሁለቱንም በአንድ ላይ የሚያቀርብ ሰው ነው።"

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፮ ውስጥ "በማንኛውም ሰው" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በማንኛውም የተመ ዘገበ ሰው" እንደዚሁም "ባለማቋረጥ ወይም በመደበኛ ሥራነት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ" በሚለው ተተክቷል።

፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ተጨምሯል፣

"፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ ተፈፃሚ የሚሆንበት ግብይት ሲከናወን እንደአስፈላጊነቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት ታክሱ ግዢውን በሚፈፀመው አካል ተይዞ ለባለሥልጣኑ ይከፈላል።"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ፊደል ተራ /ሀ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ /ሀ/ ተተክቷል፣

"ሀ. ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ የመኖሪያ ቤት ሽያጭና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፣"

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፮/ ውስጥ "የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ድንጋጌ" ተብሎ የተጠቀሰው ተሰርዞ "የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ" በሚለው ተተክቷል፣

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፯/ ውስጥ "የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ድንጋጌ" ተብሎ የተጠቀሰው ተሰርዞ "የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ድንጋጌ" በሚለው ተተክቷል።

፰/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፰/ ውስጥ "የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ/፭/ ድንጋጌ" ተብሎ የተጠቀሰው ተሰርዞ "የአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ድንጋጌ" በሚለው ተተክቷል።

2/ The following new Sub-Article (25) and (26) are added under Article 2 of the Proclamation:

"25/ 'sales register machine' means a cash register machine or a point of sale machine;

26/ 'supplier' means a person who supplies sales register machine or supplies both in one to tax payers."

3/ The phrase "any person" also the phrase "activity which is carried on continuously or regularly" in Article 6 of the Proclamation are repealed and replaced by "any registered person" and "activity whether or not carried on continuously or regularly".

4/ The following new sub-article (5) is added following sub-article (4) of Article 7 of the Proclamation:

"5/ In the case of transactions to which sub-article 1(a) of this Article is applicable, the tax shall be withheld and be paid to the Authority by the buyer in accordance with directives issued, as may be necessary, by the Ministry of Finance and Economic Development."

5/ Paragraph (a) of sub-article (2) of Article 8 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new paragraph (a):

"a) the sale o f a dwelling used for a minimum of two years, or the lease of a dwelling:"

6/ The reference to "Article 4, sub-article 3" in sub-article (6) of Article 11 of the Proclamation is repealed and replaced by "sub-article (2) of Article 4 of this Proclamation".

7/ The reference to "Article 4, sub-article (4)" in sub article (7) of Article 11 of the Proclamation is repealed and replaced by " sub-article (3) of Article 4 of this Proclamation".

8/ The reference to "Article 4, sub-article 5" in sub-article (8) of Article 11 of the Proclamation is repealed and replaced by "sub-article (4) of Article 4 of this proclamation".

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተተክቷል።

"፫. ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ የተመለከተው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው ወር እስከ መጨረሻ ቀን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ የተመለከተው ጊዜ በተጠናቀቀበት ወር እስከ መጨረሻ ቀን ለምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብና መመዝገብ አለበት።"

፲/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተተክቷል፣

"፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፮/ እና /፯/ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሂድ ሰው ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት። ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት አይችልም።"

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተሰርዞ ንዑስ አንቀጽ /፬/፣ /፭/፤ /፮/ እና /፯/ እንደ ቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ /፫/፣ /፬/፣ /፭/ እና /፮/ ሆነዋል።

፲፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተተክቷል፣

"፩/ እያንንዳንዱ የተመዘገበ ሰው፣

ሀ/ በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ግብር ባለሥልጣኑ ዘንድ በመቅረብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ወይም ባለሥልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ማስ ታወቅ፣ እና

ለ/ ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ለባለሥልጣኑ ወይም ባለሥል ጣኑ ለወከለው ሰው ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ታክሱን መክፈል አለበት።"

፲፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች /፫/፣ /፬/ እና /፭/ ተጨምረዋል፣

9/ Sub-article (3) of Article 16 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article (3);

"3/ A person required to register for VAT shall file an application for registration and get registered no later than the last day of the month after the end of the period specified in sub-article 1(a) of this Article, or the last day of the month in which the period specified in sub-article 1(b) of this Article ended."

10/ Sub-article (1) of Article 22 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub-article(1):

"1/ Except as otherwise provided in sub-articles (6) and (7) of this Article, a person registered for VAT and carries out a taxable transaction shall be required to simultaneously issue a VAT invoice to the person who receives the goods or services. A person who is not registered for VAT may not have the right to issue a VAT invoice."

11/ Sub-article (3) of Article 22 of the Proclamation is repealed and sub-articles (4), (5), (6) and (7) are re-numbered as sub-articles (3), (4), (5) and (6) respectively.

12/ Sub-article (1) of Article 26 of the Proclaimation is repealed and replaced by the following new sub-article(1):

"1/ Every registered person shall be required to:

a) file a VAT return with the Authority by appearing in person, or through electronic filing or through a third party delegated by the Authority for each accounting period, whether or not tax is payable in respect of that period; and

b) simultaneously pay the tax to the Authority or to the person delegated by the Authority by the deadline for filing the VAT return for every accounting period."

13/ The following new sub article (3), (4) and (5) are added under sub article (2) of Article 30 of the Proclamation:

"፫/ በታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ በመገኘት ምርመራ ለማድረግ ሥልጣን የተሰጣቸው የባለሥልጣኑ ሠራተኞች ማናቸውንም ሕገ ወጥ ደረሰኝ ወይም የሂሳብ ሰነድ ወይም የሂሳብ መዝገብ ካገኙ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያስፈልግ ሕገወጥ የሆነውን ደረሰኝ ወይም ሰነድ መያዝ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ የተያዘ ወይም የተገኘ ሰነድ በማስረጃነት በፍርድ ቤት ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል።

፬/ ሕገወጥ ደረሰኞችን ወይም ሰነዶችን ለመስ ጠት ፍቃደኛ ባልሆነ ግብር ከፋይ ላይ የፖ ሊስ ኃይል በመጠቀም ማስገደድ ይቻላል።

፭/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ አፈ ፃፀም በባለሥልጣኑ ሠራተኛ ትብብር የተጠየቀ ማናቸውም የፖሊስ ኃይል አባል የመተባበር ግዴታ አለበት።"

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፪ ተተክቷል፣

"፵፪/ <u>መቀጫን ስለማንሳት</u>

፩/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚነሳው መቀጫ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ መሠረት የሚ ታሰበውን ወለድ አይጨምርም።"

፲፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ውስጥ "የሚፈለግበትን ታክስ ካልከፈለ" ከሚለው ሐረግ ቀጥሎ "ወይም ይግባኝ ካላቀረበ" የሚል ሐረግ ተጨምሯል።

፲፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፭ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/፣ /ለ/፣ /ሐ/ እና /መ/ የንዑስ አንቀጽ /፩/ ፊደል ተራ /ሀ/፣ /ለ/፣ /ሐ/ እና /መ/ ሆነው የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተጨምሯል፣

"፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ አፈጻጸም "ሀሰተኛ ደረሰኝ" ማለት በባለ ሥልጣኑ ሳይፈቀድ የታተመ ወይም በኮምፒውተር የተዘጋጀ ደረሰኝ ወይም የግዢውን ወይም የሽያጩን ሂሣብ ለማሳነስ ወይም ለመጨመር በማሰብ ወይም በቸልተኛነት በሰነዱ ላይ አሀዝ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ በማ ተም ወይም በማባዛት ወይም ሁሉንም ቅጂዎች እንደበራሪ መጠቀም ወይም የሚፈቀደው የታክስ ተቀናሽ ወይም የተመላሽ ሂሣብ እንዲጨምር ወይም የማይገባውን ተመላሽ ለማግኘት ወይም ሌላ ማናቸውም የማጭበርበር ተግባር ለመፈጸም የተዘጋጀ ሰነድ ነው።"

"3/ Officers of the Authority duly authorized to carryout investigations at the business place of a taxpayer may, without the need to have court order, seize any illegal vouchers, documents or books of account they encounter. Documents seized or obtained in such a way shall be admissible evidence in court.

4/ Police force may be used against a taxpayer not willing to hand over illegal vouchers or documents.

5/ For the purpose of implementing the provisions of sub article (3) of this Article, any member of the police force shall have the duty to cooperate with the officer of the Authority when requested."

14/ Article 42 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 42:

**"42. <u>Waiver of Penalty</u>**

1/ Administrative penalties may be waived in accordance with directive issued by the Authority.

2/ Administrative penalties waived in accordance with sub article (1) of this Article may not include interest charges computed in accordance with Article 47 of this Proclamation."

15/ The phrase "or appealed against its decision" is added at the end of sub article (2) of Article 43 of the Proclamation.

16/ Sub articles (a), (b), (c) and (d) of Article 45 of the Proclamation are renumbered as paragraphs (a), (b), (c) and (d) of sub article (1) and the following new sub article (2) is added:

"2/ For the purpose of implementing the provisions of sub article 1(b) of this Article, "incorrect invoice" means printed or computer generated receipt not authorized by the Authority, or a document containing an increase or decrease in its figures with the intention to increase or decrease the actual purchase or sales amount or as a result of negligence, or prepared by printing or duplicating receipts with identical numbers or by use of copies of all receipt or by any fraudulent means for increasing tax credit or tax refund or to get tax refund while being not entitled to it or for any other similar purpose."

፲፯/ ከአዋጁ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ተጨምሯል፣

"፭/ ማናቸውም ታክስ ከፋይ በማንኛውም የሂሳብ ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ግብ ይት ባይኖረውም የታክስ ማስታወቂያ ካላቀረበ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬/ሀ/ መሠረት ይቀጣል።"

፲፰/ ከአዋጁ አንቀጽ ፵፯ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፵፯ሀ፣ ፵፯ለ እና ፵፯ሐ ተጨምረዋል፣

"፵፯ሀ **የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጮ**

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፣

፩/ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

፪/ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

፫/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ብር ፩፻ሺ ይቀጣል፣

፬/ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል ከፈጠረ ወይም በመሳሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ካላስደረገ ብር ፳፭ሺ ይቀጣል፣

፭/ በንግድ ሥራው ለሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጎን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ የተመዘገቡ ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር ፳፭ሺ ይቀጣል፣

17/ The following new sub article (5) is added after sub article (4) of Article 46 of the Proclamation:

"5/ Any person who is registered for VAT and fails to file a VAT return for each accounting period, whether or not tax is payable, shall be liable for a penalty imposed in accordance with sub article 4(a) of this Article."

18/ The following new Article 47a, 47b and 47c are added after Article 47 of the Proclamation:

"47a. **Penalties for Failure to Meet Requirements of the use of Sales Register Machines**

Any person who has the obligation to use sales register machine shall be liable for a penalty of:

1/ Birr 50,000 if found using sales register machine or point of sales machine software not accredited or registered by the Authority;

2/ Birr 50,000 for carrying out transactions without receipt or invoice or for using any other receipt not generated by a sales register machine except at the time the machine is under repair;

3/ Birr 100,000 if caused damage to or change of fiscal memory or attempts to cause damage to or change of fiscal memory;

4/ Birr 25,000 for obstructing inspection of the audit system of a sales register machine by officer of the Authority or for failure to have annual machine inspections performed by a service center;

5/ Birr 25,000 for not having a valid service contract with an authorized service center for a sales register machine in use, or for using the sales register machine without connecting to the terminal, or for not keeping the inspection booklet besides the sales register machine, or for issuing refund receipts without properly recording the return of goods or customers' request for refund in the refund book;

፮/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በስርቆት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ብልሽት ባጋጠመው በሁለት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፲ሺ. ይቀጣል፣

፯/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር ፶ሺ. ይቀጣል፣

፰/ የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር ፳፭ሺ. ይቀጣል፣

፱/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም ላይ በሚውልበት የንግድ ሥራ ቦታው፣

ሀ/ የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግዱ ሥራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የዕውቅና እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣

ለ/ "የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኛው የመስጠት ግዴታ አለባቸው" የሚል ማስታወቂያ፣ እና

ሐ/ "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል ጽሁፍ ያለበት ማስ ታወቂያ፣ በግልጽና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር ፲ሺ. ይቀጣል፣

፲/ ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍት ዌር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ባልሰጠው ሰው እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር ፴ሺ. ይቀጣል።

**፵፯ለ የአቅራቢነት ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ**

ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፣

6/ Birr 10,000 for failure to inform the Authority and the machine service center within three days of the termination of a sales register machine use due to theft or irreparable damage, or within two hours for failure to report machine malfunction due to any other causes;

7/ Birr 50,000 for failure to notify the Authority the correct place of business the sales register machine is in use;

8/ Birr 25,000 for failure to notify the Authority change of name or address or for failure to notify the Authority and the Service Center three days in advance in cases of termination of business;

9/ Birr 10,000 for failure to put a conspicuous notice containing one or all the following information at a place where the machine is installed:

a) name of the machine user, trade name, location of trade, taxpayers' identification number, accreditation and permit numbers for the sales register machine;

b) text stating that "in case of machine failure sales personnel must issue manual receipts authorized by the Authority";

c) text that reads "Do not pay if a receipt is not issued";

10/ Birr 30,000 for changing or improving a point of sales machine software by a person not accredited by the Authority.

**47b. Penalties for Failure to Observe Supplier's Obligations**

Any person who is accredited and permitted for the supply of sales register machine or soft ware shall be liable for a penalty of:

፩/ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፩፻ሺ ይቀጣል፣

፪/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ብር ፭፻ሺ ይቀጣል፣

፫/ ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምዝገባ ከባለሥልጣኑ የመሣሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሣሪያ መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካልለጠፈ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

፬/ በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም ስለ መሣሪያው አጠቃቀም በሚያብራራው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር ፩፻ሺ ይቀጣል፣

፭/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመሰረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ የአገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለባለሥልጣኑ አስቀድሞ ካላስታወቀ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

፮/ ውል ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

**፵፯ሐ** **የአገልግሎት ማዕከል ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ**

ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል፣

፩/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፊሲካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፳ሺ ይቀጣል፣

1/ Birr 100,000 for failure to notify change of business address to the Authority;

2/ Birr 500,000 for selling a sales register machine not accredited by the Authority;

3/ Birr 50,000 for failure to get a machine registration code for each sales register machine from the Authority or for not affixing the machine code stickers on a visible part of the machine;

4/ Birr 100,000 for failure to notify to the Authority in advance any change made to the sales register machine in use or for inserting or adding incorrect information or for omitting the correct information from the manual that guides the use of sales register machine;

5/ Birr 50,000 for failure to notify the Authority in advance or for not being able to replace, within three days of the request made by a service center, sales register machine lost due to theft or sustained irreparable damage;

6/ Birr 500,000 for failure to keep information about service centers with which it has signed agreements or for failure to notify the Authority about contracts terminated or newly entered agreements with service centers.

**47c.** **Penalties for Failure to Observe Sales Register Machine Service Center's Obligations**

Any Sales Register Machine Service Center shall be liable for a penalty of:

1/ Birr 20,000 for failure to report to the Authority within two days of change of the fiscal memory of a sales register machine;

፪/ ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር ፳ሺ. ይቀጣል፣

፫/ አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠውና በባለሥልጣኑ ዘንድ ሳይመዘገብ በሥራ ላሰማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር ፶ሺ. ይቀጣል።"

፲፱/ ከአዋጁ አንቀጽ ፶ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፶ሀ፣ ፶ለ፣ ፶ሐ፣ ፶መ፣ ፶ሠ፣ እና ፶ረ፣ ተጨምረዋል፣

"፶ሀ. **ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት አለመመዝገብ**

ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሳይመዘገብ የተገኘ ግብር ከፋይ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፲ሺ. እስከ ብር ፶ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮና ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።

፶ለ. **የተጨማሪ እሴት ታክስ ባልሆነ ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ማካሄድ**

፩/ ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ያለተጨማሪ እሴትታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያካሂድ ከተገኘ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፲ሺ. በማያንስ እና ከብር ፩፻ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተጠቀሰው ሕገወጥ ደረሰኝ ላይ በተመለከተው የገንዘብ መጠን መሠረት መከፈል የነበረበት ታክስ ከብር ፩፻ሺ. በላይ ከሆነ የሚጣለው የገንዘብ ቅጣት የታክሱን መጠን ያህል ይሆናል።

2/ Birr 20,000 for failure to perform annual technical inspections on sales register machines that are under contract;

3/ Birr 50,000 for deploying every person not certified by the supplier and not registered by the Authority;"

19/ The following new Articles 50a, 50b, 50c, 50d, 50e and 50f are added after Article 50 of the Proclamation:

"50a. **Failure to Register for VAT**

Any taxpayer who is required to register for VAT commits an offence if found not complying with such obligation and shall, upon conviction, be punished with a fine of not less than Birr 10,000 and not more than Birr 50,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years.

50b. **Failure to use VAT Invoice**

1/ Any person who is registered for VAT commits an offence if carries out transactions without VAT invoice and shall, upon conviction, be punished with a fine of not less than Birr 10,000 and not more than Birr 100,000 and imprisonment for a term of not less than two years and not more than five years.

2/ Where the tax payable on the basis of the amount shown on the illegal invoice referred to in sub article (1) of this Article is in excess of the Birr 100,000 the fine shall be equal to the tax amount

**፶ሐ. ያልተፈቀደ ደረሰኝ መጠቀም ወይም ማተም**

ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጥ በኮምፒውተር የተዘጋጀ ደረሰኝ ወይም ደረሰኝ በማሳተም የተጠቀመ ወይም የደረሰኝ ሕትመት አገልግሎት የሰጠ ሰው ጥፋተኝነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፲ሺ እስከ ብር ፩፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ያስቀጣል።

**፶መ. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት ስለሚፈጸም ጥፋት**

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው:-

፩/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተ ሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከተጠቀመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

፪/ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

፫/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የፊሲካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

፬/ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል የፈጠረ ወይም በመሣሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላስደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

**50c. Un authorized Use or Print of Receipt**

Any person commits an offence if uses unauthorized computer generated or printed receipts or provides the service of printing unauthorized receipts and shall, upon conviction, be punished with a fine of not less than Birr 10,000 and not more than Birr 100,000 and imprisonment for a term of not less than two years and not more than five years.

**50d. Violations of the Requirements of the use of Sales Register Machines**

Any person who has the obligation to use sales register machine:-

1/ commits an offence if found using a sales register machine not accredited or registered by the Authority and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

2/ except at the time the sales machine is under repair, commits an offence if carried out transactions without receipt or invoice or used any other receipt not generated by a sales machine and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

3/ commits an offence if caused damage or change to the fiscal memory of a sales register machine or attempts to cause damage or change to the fiscal memory and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;

4/ commits an offence if obstructed inspection of the audit system of a sales register machine by officer of the Authority, or if failed to have annual machine inspections performed by a service center and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than six months and not more than one year;

፭/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የሚገኝበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

## ፶ሠ. በአቅራቢያዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው:-

፩/ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

፪/ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፣

፫/ በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም በመሣሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

## ፶ረ. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከልና ሠራተኞች የሚፈጸሙ ጥፋቶች

፩/ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውንና በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

5/ commits an offence if failed to notify to the Authority the correct business address where a sales register machine is in use and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than six months and not more than one year.

## 50e. Offences by Suppliers

Any person who is accredited and registered to supply sales register machines:

1/ commits an offence if failed to report to the Authority a change of business address and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

2/ commits an offence if sold a sales register machine not accredited by the Authority and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;

3/ commits an offence if failed to notify the Authority in advance any change made to the sales register machine in use, or if inserted incorrect information to or omitted the correct information from the manual that guides the use of sales register machine and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five year.

## 50f. Offences by Sales Register Machine Service Centers and their Personnel

1/ Any sales register machine service center commits an offence if deployed a service personnel that is not certified by the supplier and not registered by the Authority and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

፪/ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማዕከሉና ያለባለሥልጣኑ ዕውቅና ከፈታታ ወይም ከገጣጠመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይበላሽ ሆን ብሎ እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድራጎቶች ከፈጸመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፭ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።"

፳/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ውስጥ "በ፪ /ሁለት/ ዓመት እስራት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት" በሚለው ተተክቷል።

፳፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ የነበሩት ንዑስ አንቀጽ /፬/ እና /፭/ ሆነው የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ ተጨምረዋል፣

"፪/ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ደንብና መመሪያዎችን በመተላለፍ፣

ሀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፈታታ ወይም የገጣጠመ ወይም የሰርቪስ ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሣሪያውን መለያ ቁጥር ያቀያየረ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚው ወይም በአገልግሎት ማዕከሉ ወይም በሠራተኛው ወይም በአቅራቢው የተፈጸመን ማናቸውንም ሕገ ወጥ አድራጎት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ፳፬ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፲ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

2/ Any personnel of a sales register machine service center commits an offence if, without the knowledge of the service center and the Authority, dismantle or assemble a sales register machine, or if deliberately removed the seals on a sales register machine or changed parts of a sales register machine not reported to have any break down, or if committed any similar act and shall, upon conviction, be punished with a fine of not more than Birr 5,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years."

20/ The phrase "imprisonment for a term of two (2) years" in sub article (1) of Article 51 of the Proclamation is repealed and replaced by "imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;"

21/ Sub articles (2) and (3) of Article 53 of the Proclamation are re-numbered as sub-articles (4) and (5) and the following new sub articles (2) and (3) are added:

"2/ Any employee of the Authority who, in violation of the rules and procedures of the use of sales register machines:

a) Dismantles or assembles a sales register machine or approves its utilization without the presence of a service personnel or changes the machine registration code; or

b) Knowingly or negligently fails to report to the Authority, within 24 hours, offences committed by the user or service center or its personnel or supplier of a sales register machine;

Commits an offence and shall, upon conviction, be punished with a fine of not less than Birr 5,000 and not more than Birr 10, 000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

፫/ የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለ በቂ ምክንያት ጉዳይን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።"

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ The Authority's officer shall be held responsible for any damage caused to a taxpayer by delaying without any good cause, the performance of his/her duty. Such employee in addition to being held liable for the damage, shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years."

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of December, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**